

# የሕዝብን ዝምታ ከፍርሃት መቁጠር ሞኝነት ነው፡፡

ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ሕዝብ ዝምታ ሊፈራው ይገባል፡፡ ሕዝቡ በተፈጥሮው ቻይ፣ በባህርይው ታጋሽ በሕልውናውም ከመጡበት እንደ አራስ ነብር ቁጡ ነው፡፡ ይህንን ሕዝብ ፍቅር ሰጥቶ መብቱን መጠብቅ፣ ማስተዳደርና ማስተዋልን ይጠይቃል፡፡ ባለፉት መንግሥታት የተፈጠሩ የታሪክ ስህተቶችን ላለመድገም ከታሪክ መማር ብልህነት ነው፡፡ ለገዢዎቻችንም ደጋግመን የምንወተውተው ይህንን ነው፡፡ የህዝብን ድምፅ ሰሙ፣ ብሶቱን ተባሱ፣ ቀርባችሁ ችግሩን ተረዱ ነው የዘወትር ጩኸታችን፡፡ ሕዝብን በመናቅ የራስን አገዛዝ ዘመን ለማራዘም የሚደረገው ሩጫ ውሎ አድሮ መሪዎችን የከፋ አደጋ ላይ እንደሚጥልና አገርንም እንደሚጎዳ ከግብፅና ከሊቢያ ክስተቶች ልንማር ይገባል፡፡

አንድ በሥልጣን ላይ ያለ መንግሥት በህዝብ ዘንድ እንዳይጠላ ካልተጠነቀቀ "መካሪ የሌለው ንጉስ . . ." እንዲሉ እድሜው ያጥራል፡፡ የህዝብን የልብ ትርታ በማዳመጥ የሚጠላውን የአገዛዝ አካሄድ ማሻሻል ተገቢነቱ አያጠራጥርም፡፡ በተለይም ከምርጫ 97 በኋላ ኢህአዴግ በህዝብ ጫንቃ ላይ የሚያሳርፈው ጫና ከአመት አመት እየከበደ መጥቷል፡፡ ቅድመ 97 ምርጫ በነበሩት የኢህአዴግ አገዛዝ አመታት ሕዝቡ በደሉን በውስጡ አምቆ፣ ስሜቱን በምርጫ ካርድ (በድምፁ) ብቻ መግለፁ ለገዢዎቻችን የማንቂያ ደወል ይመስለኛል፡፡ በዚያን ዓመት ነበር ኢህአዴግ ያበቃለት፤ በአገራችን እውነተኛ ዴሞክራሲ የሰፈነ ቢሆን ኖሮ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ሲደረግ ለማየት የታደልን የ21ኛው ክ/ዘመን ኢትዮጵያዊ ትውልድ እንሆን ነበር፡፡ የኢህአዴግ መሪዎችም ስማቸውና ግብራቸው ከመቃብር በላይ ሲዘከር ይኖር ነበር፡፡ ግና አልሆነም፡፡ "የሕይወት መስዋዕትነትን ከፍለን ያገኘነውን ሥልጣን በብጣሽ የምርጫ ወረቀት አንሰጥም" በሚል አምባገነን አስተሳሰብ የህዝብ ድምፅ በአደባባይ ተሻረ፡፡

"ከፉ ጎረቤት እቃ ያስገዛል" እንዲሉ በምርጫ 97 ሕዝቡ በቅንጅት ማኒፌስቶና የምርጫ ቅስቀሳ ለምን እንደተማረከ መማር ለኢህአዴግ ይጠቅመው ነበር፡፡ የራሱንም ጓዳ እየፈተሸ ያሉበትን ችግሮች ግን መንቀስ አልቻለም፡፡ ዛሬም ከህዝብ ጋር የሚያቃቅረውን ፖሊሲ እየነደፈና የዴሞክራሲን ጭላንጭል በፅልመት እየጋረደ ራሱን ለአውራ ፓርቲነት ማብቃቱ "የውሃ ጠብታ አለትን ትሰረስራለች" እንዲሉ የኋላ ኋላ እየጨመረ የመጣውን የሕዝብ ብሶት ለመመለስ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

ምርጫ ሲደርስ ኢህአዴግ እንደ እድር ነጋሪ በየሰፈሩ በሚያሰማራቸው ካድሬዎቹ (ዘመናዊ ቆራሌዎች) አማካኝነት ሕዝብን በአንቀልባ ለማዘል ይዳዳዋል፡፡ የጨረቃ ቤት የሚል ስያሜ የተሰጣቸው ሕገወጥ ግንባታዎች ሕጋዊ እንደሚሆኑና እንደሚፀድቁ ይለፍፋል፡፡ ወጣቶችና ሴቶች በጥቃቅን አነስተኛ ተደራጅተው እንዲንቀሳቀሱ ጥሪ ይደረጋል፡፡ በየመስሪያ ቤቱ ህዝብ ለአቤቱታ ከመጣ ጉብ (ቂጥጥ) እየተባለ ይስተናገዳል፡፡ ብቻ ምኑ ቅጡ! ይሄ ሁሉ መራጩ ህዝብ ካርዱን እንዳይነፍገው ለመሸንጋገል ነው፡፡ የዶሮ ማታው አይነት የኮሶ ማጠጫ የማይተገበር ቃል ኪዳን፡፡ ምርጫው እንዳለፈ አፍንጫችሁ ላሱ ይላል፤ ከዚህ በኋላ፡፡ ካቢኔዎቹ አካፋና ዲጂኖ ያነገቡ ወዛደሮችን ከኋላ አስከትለው ሕዝቡ በችግር እየተጠበሰ የቀለሳትን ጎጆ በጠራራ ፀሐይ ይንዷታል፡፡ ያደራጃቸው ማህበራት በችግር ሲቆላለፉ እያየ ፊቱን ያዞራል፡፡ በየመስሪያ ቤቱ የሚስተዋለው ቢሮክራሲ ጭራሽ ብሶበት ሕዝብ ሲጉላላና ሲያጉረመርም ይታያል፡፡ ይህን ጊዜ ሕዝብ ቂም

ያረግዛል፣ ጥርሱን ይነክሳል፡፡ "አይነጋ መሰሏት . . ." እያለ ይዝታል፤ በቀጣዩ ምርጫ ካርድ በመንፈግ ሊበቀለው አያስብም ማለት የዋህነት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ዴሞክራሲ ባልሰፈነባቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገራት ተቀናቃኞች በምርጫ አሸንፈው ስልጣን ለመያዝ ሲበቁ ማየት የሕልም እንጀራ እየሆነብን መጥቷል፡፡ ተስፋችንም እየጨለመ ነው፡፡ ሕዝቡ ግን ቂም እንዳረገዘና እህህ እንዳለ ማዝገሙ የኢህአዴግን ተጠይነት እያጎነው መጥቷል፡፡

የመልካም አስተዳደር እጦትና ሙስና እድሜ ማሳጠሪያዎች ናቸው፡፡ በአንድ የመንግስት አስተዳደር ውስጥ የመልካም አስተዳደር መስፈን ለገዢው አካል ዋስትናን ይሰጣል፡፡ ሕዝብ ባግባቡ የሚያስተዳድሩት፣ቀርበው ለጥያቄው ምላሽ የሚሰጡት፣ ዝቅ ብለው የሚያገለግሉት አስተዳዳሪዎች በየደረጃው ሲሾሙለት አሜን ብሎ በፍቅር ይገዛል፡፡ ኢህአዴግ ግን በዚህ ረገድ እጅግ የገዘፈ ችግር አለበት፡፡ ሹመኞቹ በብቃት ማነስ የእውር ድንብራቸውን ሲጓዙ እና በየቀኑ በሚደረጉ አሰልቺና ፀያፍ ግምገማዎች ካድሬዎቹ ከስልጣን ሲወርዱና ሲወጡ ማየት የዘመነ ኢህአዴግ ተውኔት ነው፡፡ ችግሩ ደግሞ ከታችኛው እስከላይኛው መዋቅር ድረስ የሚታይ ነው፡፡ ገዢው ፓርቲ በየደረጃው የሚያስቀምጣቸው የሕዝብ አስተዳዳሪዎች ነጋ ጠባ ህዝብን ለምሬት የሚዳርጉት ከሆነ ኢህአዴግ ዕድሜው እንደሚያጥር ሊገነዘብ ይገባል፡፡

በሌላ በኩል የመልካም አስተዳደር ችግር ለሙስና በር የሚከፍት ይሆናል፡፡ በጥቅማ ጥቅም እየተደለሉ ፍትህን ማዛባት የከፋ አደጋ ያስከትላል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ በቀን አንድ ጊዜ ለመመገብ በተቸገረበት በአሁኑ ሰዓት ጥቂት የኢህአዴግ ሹመኞች ከቀበሌ እስከ ፌዴራል ድረስ የአገርን ሀብት እየተቀራመቱ ኑሮአቸውን ሲያደላድሉ ማየት እንደ ባህል እየተቆጠረ መጥቷል፡፡ ኢህአዴግም ሚስጥሩን አፍኖ እንጂ ሙስና ከቁጥጥሩ በላይ ሆኖበታል፡፡ በቅርብ ጊዜ ውስጥ በአለም አቀፍ ደረጃ የወጡ መረጃዎች እንዳመላከቱት በየጊዜው በባለሥልጣናትና በኢንቬስተሮች መካከል በሚሰሩ የረቀቁ ወንጀሎች እስከ 11.7 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ከአገር መውጣቱ ተዘግቧል፡፡ ይህ አስደንጋጭ አሀዝ ከመገታት ይልቅ በየአመቱ እየጨመረ መምጣቱ ሁኔታውን ውስብስብ አድርጎታል፡፡ ከዘመኑ ሹመኞች (ከቀበሌ እስከ ሚ/ር ማዕረግ ከተሾሙት) በሙስና ያልተነካካን ሰው ማግኘት እጅግ አስቸጋሪ ነው፡፡ ኢህአዴግም ሹመኞችን በሙስና ሰበብ በህግ ፊት የሚያቀርበው ግለሰቦቹ ፖለቲካዊ ችግር የሚፈጥሩ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ይሄውም ሰሞኑን እየሰማን ያለው የሙስና ቅሌት ይሄ ደግሞ የገዢው መደብ በተለይም የአቶ በረከት ክፉ አመል እንደሆነ ከአቶ ታምራት፣ ከአቶ ስዬ አብርሃ የግፍ ውንጀላ መገንዘብ የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ትናንት በየአካባቢው የሚያውቀው የኢህአዴግ ሹመኛ ከብርሃን ፍጥነት በመጠቀ ሁኔታ ባለ ትላልቅ ፎቆችና ባለ ዘመናዊ መኪና ባለቤት ሲሆን ሲያየው "ምን ሠርቶ አገኘ?" የሚለውን ጥያቄ እያነሳ ይገኛል፡፡ እውነት ለመናገር በስመ ታጋይና ተጋዳላይ ጥቂት የትግራይ ተወላጆች እና ጀሌዎቻቸው ቁንጮ ኢንቬስተሮች መሆናቸው አነጋጋሪ ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ የህዝቡን አንጡራ ሀብት በመዝረፍ ባፍንጫቸው ቅቤ እየጠጡ የሚንደላቀቁ ሹማምንት ቅጥ ያጣ ኑሮ ሲኖሩ የሚያየው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ነኝ ለማለት አይደፍርም፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያዊ ለመሆን የሥርዓቱን የነቀዘና በሙስና የበከተ አካሄድ ለመታገል ግድ ይላልና፡፡ ሕዝቡ ተቃውሞውን በአደባባይ ማሰማቱ አይቀርም፡፡

**ኢትዮጵያ በክብር ለዘላለም ትኑር!**

ዳዊት ገሰሰ ( ከኖርዌይ)

**http://andenatethiopia2012.blogspot.no**

**Revolution4ethiopia@gmail.com**